# <u>ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡</u>
# <u>የኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና ጸሎት፡፡</u>

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! *“እናንተ ስትጸልዩ፡ 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!' በሉ!”* ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትክልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምክልን፤ ጺጋህንም ሰጠኸን፡፡ ስለዚህ እናመሰግንሃለን፡፡

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጺጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን፡፡ ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ፡፡ ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ፡፡ መንግሥትህም መጣችልን፡፡ በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም እንዲሁ ኾነ፡፡

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን፡፡ ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን፡፡ በእርሱም፡ ኃጢኣታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን፡፡ እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን፡፡

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጺጋ አደልኸን፡፡

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን፡፡

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጺጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን፡፡

*“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”* በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢኣትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን፡፡

*ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡*